የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 20
ADDIS ABABA - 10th February, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የአደገኛ ዝቃጮች ድንበር ዘለል ዝውውርን እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የወጣውን የባዝል ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፩ሺ፪፻፴፰

## CONTENTS

Proclamation No. 192/2000
Basel Convention on the Control of the Transboundary Movements of Hazardous Wastes and their Disposal Ratification Proclamation.......... Page 1238

## አዋጅ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፺፪
## የአደገኛ ዝቃጮች ድንበር ዘለል ዝውውርን እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የወጣውን የባዝል ኮንቬንሽን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

የአደገኛ ዝቃጮች ድንበር ዘለል ዝውውርን እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የባዝል ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ. ማርች ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. የወጣ ስለሆነ ፤

ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ፤

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአደገኛ ዝቃጮች ድንበር ዘለል ዝውውርን እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የወጣው የባዝል ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፺፪/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. ኮንቬንሽኑ ስለመጽደቁ

የአደገኛ ዝቃጮች ድንበር ዘለል ዝውውርን እና አወጋገድን ለመቆጣጠር እ.ኤ.አ. ማርች ፳፪ ቀን ፲፱፻፹፱ የወጣው የባዝል ኮንቬንሽን ጸድቋል ።

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE BASEL CONVENTION ON THE CONTROL OF THE TRANSBOUNDARY MOVEMENTS OF HAZARDOUS WASTES AND THEIR DISPOSAL

WHEREAS, the Basel Convention on the Control of the Transboundary Movements of Hazardous Wastes and their Disposal has been adopted on the 22nd day of March, 1989;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Convention at its session held on the 10th day of February, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
   This proclamation may be cited as the "Basel Convention on the Control of the Transboundary Movements of Hazardous Wastes and Their Disposal Ratification Proclamation No. 192/2000."

2. *Ratification of the Convention*
   The Basel Convention on the Control of the Transboundary Movements of Hazardous Wastes and their Disposal, adopted on the 22nd day of March, 1989, is hereby ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ኃላፊነት

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ መስተዳድር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ኮንቬንሽኑ በሥራ ላይ እንዲውል የሚያደርግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Responsibility of the Environmental Protection Authority*

The Environmental Protection Authority is hereby authorized to undertake, in cooperation with the appropriate Federal, Regional and City Administration government organs, all acts necessary for the implementation of the Convention.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 10th day of February, 2000.

Done at Addis Ababa, this 10th day of February, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE